# ለጎረቤት ሶማሊያ መረጋጋት የሠራዊታችን የማይተካ ሚና

ወንድይራድ ኃብተየስ **03-16-17**

የአፍሪካ ቀንድ እየተባለ የሚጠራው የአህጉራችን ክፍል ኢትዮጵያን፣ ሶማሊያን፣ ኤርትራንና ጁቡቲን የሚያጠቃልል ቀጣና ነው፡፡ በእንግሊዝ እና በጣሊያን ቀኝ ግዛት ሥር የነበሩት የሶማሊያ ግዛቶች እ.ኤ.አ በ 1960 ነጻነታቸውን ሲቀዳጁ፤ በእንግሊዝና በጣሊያን አገዛዝ ሥር የነበሩትን የሰሜንና የደቡብ ሶማሊያ ሁለት ግዛቶችን አንድ ላይ በማዋሃድ ሶማሊያን መሠረቱ፡፡

ከሶማሊያ መመሥረት በኋላ አገሪቱን ለረጅም ጊዜ የመራው የመሐመድ ዚያድባሬ መንግሥት ነው፡፡ ይህ መንግሥት ለሶማሊያ ህዝብ መሻሻልና ብልፅግና ከመሥራት ይልቅ፤ ታላቋን ሶማሊያ የመመስረት አባዜ ተጠናውቶት በኬንያ፣ በጁቡቲና በኢትዮጵያ መንግሥት ሥር ያሉ ትውልደ-ሶማሌዎችን በራሱ አገዛዝ ሥር ለመጠቅለል ተንቀሳቅሷል።

እናም እ.ኤ.አ በ 1964 በአፄ ኃይለስላሴ መንግሥት፣ ኋላ ላይም እ.ኤ.አ በ 1977 በደርግ መንግሥት ላይ ጦርነት አውጇል— በወቅቱ በነበረው የአገራችን ሠራዊት ድባቅ ተመቶ ተመለሰ እንጂ፡፡

ወረራዎቹን ተከትሎም የዚያድባሬ መንግሥት ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ውድመት ደርሶበታል፡፡ በዚህም ሣቢያ በዚያች አገር በተፈጠሩ አንጃዎች ምክንያት አገሪቱ መንግሥት አልባ ልትሆን ችላለች። መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የሽብርተኝነት አደጋ አገራችን ላይ የተደቀነው ከዚያድባሬ መንግሥት መፈረካከስ ማግሥት በኋላ ነው፡፡

ኢትዮጵያና ሶማሊያ የረጅም ጊዜ ታሪካዊና ባህላዊ ግንኙነት ያላቸው እህትማማች አገሮች ናቸው፡፡ ህዝቦቻቸውም በታሪክ፣ በባህል፣ በቋንቋና በኃይማኖት የተሳሰሩ ናቸው፡፡ እርስ በርሳቸውም ተዋልደዋል፣ አንዱ በሌላኛው ውስጥ

የህይወት ቁርኝትን ፈጥሯል። ይህ ሥር የሰደደ የግንኙነታቸው ድርም በየትኛውም ኃይል ሊበጣጠስ የማይችል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አገራቱ ያላቸው የመልከዓ ምድራዊ አቀማመጥና የሚጋሩት ረጅም ድንበር ለንግድ ግንኙነታቸው አመቺ ሁኔታ የሚፈጥር ነው፡፡

ለሁለት አሥርት ዓመታት መንግሥት አልባ ሆና የቆየችው ሶማሊያ፤ ህዝቦቿ በአክራሪ አሸባሪ ቡድኖች ሠላምና መረጋጋት ሲያጡ ከለላቸውና መከታቸው አድርገው የሚመርጧት ኢትዮጵያ መሆኗም የአገራቱን ጥብቅ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ሁነኛ አመላካች ነው፡፡

እርግጥም ወንድም የሆነው የሶማሊያ ህዝብ በአሸባሪዎች እንግልት ሲደርስበት ሁለተኛው አገሩ ወደሆነችው ኢትዮጵያ ከመሰደድ ውጭ አማራጭ አልነበረውም፡፡ ለነገሩ ሁለቱ ህዝቦች የተጋመዱበት ረጅም የወንድማማችነትና የእትማማችነት ሰንሰለት ሁሉን አቀፍ በመሆኑ፤ የትስስራቸውን ደርዝ በዚህ አጭር ፅሑፍ መዘርዘር አይቻልም— አንዱን ጥሎ ሌላውን ማውሳት የእውነታውን ፍካት ሊያደበዝዘው ይችላልና።

ዳሩ ግን መንግሥት አልባ የነበረችው የያኔዋ ሶማሊያ ሠላምና መረጋጋት አጥታ የአሸባሪዎች መናኸሪያ ሆና ቆይታለች— ምንም እንኳን ከጥቂት ዓመታት በፊት ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶት በአሁኑ ወቅት አንፃራዊ መረጋጋት ቢታይባትም፡፡

በዚህች አገር የመሸጉና ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የተሰባሰቡ አክራሪዎችና አሸባሪ ቡድኖች የሶማሊያ ህዝብን ብቻ ሳይሆን፣ ቀጣናውን በማተረማመስ ጭምርም በርካታ የሽብር አደጋዎችን ማድረሳቸው አይዘነጋም፡፡

አሸባሪ ኃይሎቹ በኬንያ፣ በሩዋንዳ፣ በኡጋንዳና በኢትዮጵያ ያደረሷቸው ተደጋጋሚ የሽብር ጥቃቶች ምንኛ አሰቃቂ እንደነበሩም እንዲሁ። በዚህም ሣቢያ ሶማሊያውያን በገዛ አገራቸው ለደህንነታቸው ዋስትና አጥተው፣ በየጎራው ያኮረፉ

የጦር አበጋዞች ህገ-ጡብመንጃን ብቸኛው አማራጭ አድርገውባቸው እንዲሁም በጎሰኝነት የመከፋፈል ጣጣ ተጭኖባቸው ለሞት፣ ለእንግልትና ለስደት ተዳርገው ኖረዋል። ከዚህ በተጨማሪም የያኔዋ ሶማሊያ ለአሸባሪ አክራሪ ቡድኖች ምቹ ምድር በመሆን የጦር መሣሪያዎች እንደ አሸን የሚለዋወጡባትና የሚቸበቸቡባት፣ አደንዛዥ እፆች ያለ ገደብ የሚዘዋወሩባት እንዲሁም ዋነኛ የኮንትሮባንዲስቶች መናኸሪያ ሆና ዘልቃለች፡፡

በአገሪቱ የመሸጉ አሸባሪ ኃይሎች የእስልምና አክራሪነትን ብሎም ኃይማኖታዊ መንግሥትን ለማስፋፋት በአፍሪካ ቀንድ ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም፡፡ ታዲያ በቀዳሚነትም በሶማሊያ የሽብር አጀንዳን ይዞ በግልፅ መንቀሳቀስ የጀመረው "አል-ኢትሃድ አል- ኢስላሚያ" የተሰኘው የሽብር ቡድን ነው፡፡ ይህ አሸባሪ ቡድን ለአፍሪካ ቀንድም ይሁን ለአገራችን ጠንቅ የሆነ አደገኛ አሸባሪ እንደነበር አይዘነጋም፡፡

"አል- ኢትሃድ አል- ኢዝላሚያ" እ.ኤ.አ በ 1984 በሶማሊያ ቡራ ላይ ፀረ- ምዕራባዊ የባህል አቋም ባላቸው "ዋሃዳት አል-ሸባብ -አል ኢስላሚያ" እና "አል-ጀምዓ አል- ኢስላሚያ" በተባሉ ቡድኖች ውህደት የተመሠረተ ነው፡፡

ቡድኑ ከመነሻው የእስልምና አንድነት ወይም የእስልምና ህብረት በሚል ጽንሰ ሃሳብ ላይ የተመሠረተ ቢሆንም ቅሉ፤ ብዙም ሳይቆይ የ"አል- ኢትሃድ" ቅርፅን ይዞ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ የቡድኑ ምሥረታ ዋነኛ ዓላማ በአፍሪካ ቀንድ እስላማዊ መንግሥት ለመመሥረት ነበር፡፡

ከዚህም በኋላ ፅንፈኛ ሆኖ ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ እ.ኤ.አ እስከ 1991 ድረስ በሶማሊያ ውስጥ በወታደራዊና በትምህርት ተቋማት ጥቃት በመሰንዘር አበክሮ ተንቀሳቅሷል፡፡ ለጥቆም የሽብር ጥቃቱን ወደ ኢትዮጵያ አዞሯል።

"አል- ኢትሃድ" የሽብር ጥቃቱን ወደ አገራችን ለማዞር የተገደደው በፑንት ላንድ ሽንፈት ከደረሰበት በኋላ እንደሆነ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ ቡድኑ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ያስቻለው በወቅቱ ኢሕአዴግ አገሪቱ በተቆጣጠረበተ ወቅት

የተረጋጋ ሁኔታ አለመኖሩን ተከትሎና ሶማሊያ በእርስ በርስ ጦርነት በታመሰችበት ወቅት ወደ ኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ከገረፉት የሶማሊያ ስደተኞች ጋር ተቀለቀቅሎ ነበር፡፡

እናም የሽብር ቡድኑ የአገራችንን የሶማሌ ክልል አብዛኛውን ቦታዎች መያዝ ችሎ ነበር፡፡ ከዚህ ባሻገርም እ.ኤ.አ በ 1992 መጨረሻ አካባቢ አስገራሚ የሽብር ጥቃት በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል መፈፀም ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ፤ እ.ኤ.አ ከ 1993 እስከ 1996 ድረስ በአዲስ አበባ በንጹኃን ዜጎች ላይ ዘግናኝ የሽብር ጥቃቶችን ከውኗል፡፡ ከዚህ በኋላ ግን ቡድኑ በመከላከያ ሠራዊታችን ብርቱ ርምጃ ተወስዶበት ከኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ሸሽቶ ወደ ያኔዋ መንግሥት አልባዋ ሶማሊያ ሊፈረጥጥ ችሏል፡፡

የሶማሊያ ቆይታው ግን አልጋ…በአልጋ አልነበረም። ወትሮም የህዝብ ድጋፍ የሌለው ማንኛውም ኃይል መሰነጣጠቁ አይቀርምና ቡድኑም በሶማሊያ ህዝብ በመተፋቱ ሣቢያ ዕጣ ፈንታው በሁለት ትንንሽ ቡድኖች መከፋፈል ነበር።

አንደኛው በወቅቱ ሶማሊያን የሸሪዓ ህግና የእስልምና መንግሥት እንደሚመራት በይፋ ያወጀው ብሎም ራሱን “የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ህብረት” እያለ የሚጠራው ፅንፈኛ ቡድን ነው። ሁለተኛው ደግሞ “ሃረካት አል-ሽባብ አል-ሙጃሂዲን” የተሰኘው የሽብር ቡድን ነው።

ከዚህ ቀደም በሶማሊያ ፌዴራላዊ መንግሥት በተያዘው ሼክ ዳሂር ሃዌይስ ይመራ የነበረው የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ህብረት ቡድን፤ ሶማሊያን ሙሉ በሙሉ ከተቆጣጠረ በኋላ በሌሎች የአፍሪካ ቀንድ አገራትም የእስልምና መንግሥትን የመመሥረት ዓላማ ያነገበ ነበር፡፡ ቡድኑ በሼክ ዳሂር ሃዌይስ አማካይነት በአገራችን ላይ የጅሃድ ጦርነት ማወጁም የሚታወስ ነው፡፡ በሰባት ቀናት ውስጥም በመዲናችን የሚገኘውን ቅዱስ አንዋር መስጊድን ለመቆጣጠር ቆርጦ ተነስቶ

እንደነበርም በወቅቱ ያወጣው የመግለጫ ዲስኩሩ ያስታውሰናል፡፡ ምንም እንኳን ዲስኩሩ ከትውስታ ውጪ ባይዘልም።

ቡድኑ በሶማሊያ የተቋቋመውንና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያለውን የሽግግር መንግሥት ገልብጦ በሶማሊያ የራሱን መንግሥት ለመመሥረት ከፍተኛ ጥረት ነበር። ዳሩ ግን ቀድሞውንም ከአል-ቃዒዳ ጋር ግንኙነት እንዳለው የሚጠረጠረው አል - ኢትሃድ የተገነጠለው አሸባሪ ድርጅት መሉ በሙሉ ዓለም አቀፋዊ ተቃውሞ ሊገጥመው ችሏል፡፡ ኋላ ላይም በኢትዮጵያ ሠራዊትና በሶማሊያ የሽግግር መንግሥት ጦር አማካይነት ድል ተመትቷል።

መከላከያ ሠራዊታችን ከ 1999 ዓ.ም እስከ 2001 ዓ.ም ድረስ በሶማሊያ በነበረው ቆይታ አክራሪና አሸባሪ ኃይሎች ከህዝቡ ይበልጥ እየተነጠሉና እየተዳከሙ ከመምጣታቸውም በላይ፤ ህዝቡም የሠላም ፍላጎቱን እየተጠናከረ መሄድ የጀመረበት ወቅት ነበር፡፡

አሸባሪዎች በህዝቡ ላይ ጥቃት እያደረሱ ሠራዊታችንን ከህዝብ ጋር ለማጋጨት ያደረጉት ጥረት መክኖ ለለውጥ አመቺ ሁኔታ የፈጠረም ነበር፡፡ ምክንያቱም የሶማሊያ ህዝብ ሠራዊታችን አሸባሪዎችን ከበታተነ በኋላ የአንፃራዊ ሠላም ባለቤት በመሆኑና ለፅንፈኞቹ አሉባልታም ሊፈታ ባለመቻሉ ነው።

ሠራዊታችን የሽግግር መንግሥቱን የፀጥታ አስከባሪ ኃይሎች ለማቋቋምና ለመገንባት ያደረገው ብርቱ ተግባርም ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አድናቆት ተችሮታል፡፡ ሠራዊታችን አገራችን የተደቀነባትን ግልፅና ድርስ አደጋ የማስወገድ ተልዕኮውን በአስገራሚ ብቃትና ዲሲፕሊን ተወጥቶ ወደ አገሩ ሲመለስ፤ ከጥቂት ወራት በኋላ በሶማሊያ የአፍሪካ ህብረት ተልዕኮን በሚወጣው ሠላም አስከባሪ ኃይል ሊተካ ችሏል፡፡

ታዲያ ከ 2002 ዓ.ም ጀምሮም የኡጋንዳና የብሩንዲ ሠላም አስከባሪ ወታደሮች በሶማሊያ ሞቃዲሾና አንዳንድ አካባቢዎች ሠላምን ለማረጋጋት ያደረጉት ጥረት ቢደነቅም፤ ጥረቱ ግን ሠላም አስከባሪው ካለው የሰው ኃይል እጥረት እንዲሁም ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለሶማሊያ ሠላምና መረጋጋት በቂ ድጋፍ ባለማድረጉ የታሰበውን ያህል ውጤት ማስገኘት ባለመቻሉ እንደገና ውጥረት መፈጠሩ የሚታወስ ነው፡፡

እናም የእስላማዊ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ህብረት ድባቅ ተመትቶ ግማሽ ኃይሉና አመራሩ ኤርትራን ምሽጉ ካደረገ በኋላ ሁለተኛው የአል-ኢትሃድ ተሰንጣቂ ቡድን የነበረውና እስከ አሁን ድረስም ሙሉ ለሙሉ ያልተወገደው "ሃረካት አል-ሸባብ አል ኢስላሚያ" ብቅ አለ፡፡ ይህ ቡድንም እንደ ሌሎቹ አሸባሪዎች ሁሉ በተቆጣጠራቸው ቦታዎች ውስጥ ያሉ ሶማሊያውያንን ቁም ስቅላቸውን ከማሳየት ባለፈ፤ በአገራችን ላይም የጀሃድ ጦርነት አውጇል።

ግና አሸባሪዎች በአገራችን ላይ የያዙትን ዓላማ ሳይለቁ ራሳቸውን በስም መቀያየር ብቻ እየሰየሙ መፈራረቃቸው በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ያደረጉትን ጥረት ከንቱ ነበር፡፡ ሆኖም በኃይል ህዝብን ከማሸበር ተግባራቸው ሊታቀቡ አልቻሉም፡፡

ታዲያ እዚህ ጋር ሳይጠቀስ የማይታለፈው ጉዳይ፤ ሶማሊያ የመሸጉት ፅንፈኞችና አሸባሪዎች ሞቃዲሾንና አካባቢዋን ተቆጣጥረው በአገራችን ላይ ግልፅና ድርስ አደጋ መደቀናቸውን ተከትሎ፣ የኢፌዴሪ መንግሥት መክሮና ዘክሮ ሰሚ ሲያጣ በአገራችን ላይ ያንዣበበውን አደጋ ለማስቀረት ሲል ብቻ ሠራዊታችን ሶማሊያ እንዲገባ ማድረጉን ነው፡፡

እናም አል-ሸባብ ሶማሊያንና የአካባቢውን አገራት ለማሸበር በግልፅ የአል-ቃዒዳ ክንፍ መሆኑን አውጆ ቀደም ሲል በዚያች አገር የተገኘው አንፃራዊ የተረጋጋ ሁኔታ መልሶ መደፍረሱ ይታወሳል።

በዚህም ሣቢያ የሽግግር መንግሥቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ዕገዛ እንዲያደርግለት ባደረገው ጥሪ መሠረት መከላከያ ሠራዊታችን ዳግም በ 2003 ዓ.ም ወደ ሶማሊያ ዘልቆ አል-ሸባብን አይቀጡ ቅጣት ቀጥቶታል፡፡

በአል-ሸባብ ደፍርሶ የነበረውን የአገሪቱን ሠላም መልሶ ወንድም ለሆነው የሶማሊያ ህዝብ አንፃራዊ በሆነ ሁኔታ ለማስገኘትና ቀጣናዊ የሥጋት ደመናን ለማስወገድ ለሁለት ዓመታት ያህል ቆይታ አድርጓል፡፡

መከላከያ ሠራዊታችን በዳግም የሶማሊያ ቆይታው አሸባሪ ቡድኑን ለማዳከም ችሏል፡፡ የሽግግር መንግሥቱንም አጠናክሯል፡፡ በምርጫ አሸንፎ አገሪቱን የሚያስተዳድር መንግሥት እንዲመሠረትም የነበረው ሚና የላቀ ነበር፡፡

ይህም ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ከዚህ አኩሪ ተግባር በኋላ ለሶማሊያ መረጋጋት ትኩረት እንዲሰጥ አድርጓል፡፡ በመሆኑም የአፍሪካ አገራት በሶማሊያ ጦራቸውን ለማሰማራት የገቡትን ቃል ተግባራዊ እንዲያደርጉ አስችሏቸዋል፡፡ በውጤቱም የኡጋንዳና የቡሩንዲ ሠላም አስከባሪዎችን ለማገዝ የጅቡቲ፣ የኬንያና የሴራሊዮን ሠላም አስከባሪዎች የአሚሶምን ተልዕኮ ማድረጉም እንዲሁ። ታዲያ እነዚህ ሠላም አስከባሪ ኃይሎች በአሁኑ ወቅት በሶማሊያ የተሻለ ሠላም ለማስፈን ተልዕኳቸውን በመወጣት ላይ ይገኛሉ፡፡